# በሀገራዊ ምክክር ሂደት አጀንዳ ለማሰባሰብ የሚደረግ የተሳታፊዎች ልየታ

## በሀገራዊ ምክክሩ ላይ በተወካይ መሳተፍ ማለት ምን ማለት ነው?

በሀገራችን ኢትዮጵያ ዓውድ በሀገራዊ ምክክሩ ሂደት በተወካይ መሳተፍ ማለት ኮሚሽኑ በክልሎች፣ በከተማ መስተዳደሮች፣ በፌደራል ደረጃ እንዲሁም በዲያስፖራው ማህበረሰብ ውስጥ በሚያደርጋቸው አጀንዳዎችን የማሰባሰብ ስራዎች ላይ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካለት ይወክሉናል ላኒቸው ሰዎች የተለያዩ ሀገራዊ አጀንዳዎችን በአደራ ሰጥተው ሃሳባቸው እንዲንፀባረቅ የሚያደርጉበት ሂደት ነው።

## በወረዳዎች (ልዩ ወረዳዎች) የሚደረግ የተሳታፊዎች ልየታ ምንድነው? ዓላማውስ?

የሀገራዊ ምክክሩ ዋነኛ ግብ እንደሀገር ያልተግባባንባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች በመለየት፤መንስኤዎቻቸውንም ነቅሰን በማውጣት፤ቁጭ ብለን በእውነትና በመመካከር ተነጋግረን የጋራ መግባባት የምንፈጥረበት ሂደት ነው። በሂደቱም የሁሉም ዜጎች ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ከ120 ሚሊዮን በላይ የሚሆንን ህዝብ በቀጥታና በአንድ ጊዜ ማሳተፍ ግን ከጊዜና ገንዘብ አኳያ አዳጋች ነው።

በመሆኑም በወረዳዎች (ልዩ ወረዳዎች) ውስጥ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙባቸውን አደረጃጀቶች እና ከዚያም ውጪ ያሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች በማሳተፍ ዜጎች ሀሳባችንን ያሰሙልናል የሚሏቸውን ሰዎች እንዲወክሉ መንገዱ ተመቻችቷል። በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለሀገር በሚደረገው ምክክር በውክልና ተሳታፊ ይሆናሉ።

በዚህም መሰረት የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮችን በወረዳ (ልዩ ወረዳ) የመለየቱ ሂደት ዋና ዓላማ በክልሎች (ከተማ መስተዳደሮች) ለሚደረጉት አጀንዳዎችን የማሰባሰብ ተግባራት ተወካዮችን ለማስመረጥ ሲሆን ለሂደቱም መሳካት የተለያዩ ተባባሪ አካላት እገዛ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

# የተሳታፊዎች ልየታ የት እና እንዴት?

የሀገራዊ ምክክሩን አጀንዳዎች ለማሰባሰብ አግባብ ሆኖ የተገኘው መንገድ ከመሰረታዊው የሕዝብ መገኛ በመነሳት ተሳታፊዎችን እየለዩ መምጣት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን ኢትዮጵያ የተደራጁትንም ሆነ ያልተደራጁትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ለማግኘት በማሰብ ሥራውን በወረዳዎች (ልዩ ወረዳዎች) ውስጥ ከሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች ማስጀመር አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በወረዳ የተለዩት የሕብረተሰብ ክፍሎች ወደ ክልል (ከተማ መስተዳድሮች) በመሄድ በክልሎች (ከተማ መስተዳድሮች) ከተወከሉ የባለድርሻ አካላት ተወካዮች ጋር በመሆን አጀንዳዎች በማሰባሰብ ሂደት ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል ደረጃም የሚወከሉ ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ ሁኔታ የሚገለጹ ቢሆንም ለሀገራዊ ምክክሩ አመቺነት የሚከተሉት አስር የሕብረተሰብ ክፍሎች (እንደ አውዱ ሊጨምርም ሊቀንስም ይችላል) በወረዳ ደረጃ ተለይተዋል፡፡

- ✓ እራሳቸውን የሚገልፁበት ዋና መተዳደሪያ ያላቸው ሰዎች (በዋናነት አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች)
- ✓ የንግድ ማህበረሰብ
- ✓ ሴቶች
- ✓ ወጣቶች
- ✓ ዕድሮች
- ✓ የማህበረሰብ መሪዎች/አባቶች/እናቶች
- ✓ የመንግስት ሰራተኞች እና የግል ድርጅት ሰራተኞች
- ✓ መምህራን
- ✓ በባህል እና በሙያቸው ምክንያት የተገለሉ
- ✓ ተፈናቃዮች (በሚገኙባቸው ቦታዎች)

ከላይ የተጠቀሱት የሕብረተሰብ ክፍሎች በኮሚሽኑ ጠያቂነት እያንዳንዳቸው 10 ሰዎችን ከየማህበረሰብ ክፍላቸው በየወረዳው ወክለው ይልካሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ለሚደረጉ የአጀንዳ ማሰባሰብ ስብሰባዎች ከላይ የተጠቀሱት

የሕብረተሰብ ክፍሎች ሁለት ሁለት ተወካዮችን ይመርጣሉ። በዚህ አግባብ ተመርጠው ከሚመጡት ተወካዮች ውስጥ ቢያንስ 30% ሴቶች (የቤተሰብ መሪ የሆኑትን ጨምሮ) ፣ 10% አካል ጉዳተኞች (በተጨባጭ ካለው ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ የሚፈጸም)፣ 20% ወጣቶች እንዲሆኑ ኮሚሽኑ በአሰራሩ ደንግጓል።

## የተሳታፊዎች ልየታ በማን?

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ስራን ራሱ የሚመራውና የሚከታተለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሂደቱ ላይ እገዛ ያደርጉልኛል ብሎ ያመነባቸውን የሚከተሉትን ሰባት ተባባሪ አካላት ለይቷል።

- ✓ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ምክር ቤት
- ✓ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት
- ✓ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር
- ✓ የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የእድሮች ማህበራት ጥምረት
- ✓ የኢትዮጵያ ሀይማኖት ተቋሟት ጉባኤ
- ✓ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች
- ✓ የወረዳ (ልዩ ወረዳ) አስተዳደር ተወካዮች

እነዚህ አካላት የሂደቱን ግልጸኝነት፣አሳታፊነት እና ተዓማኒነት በመታዘብና በማረጋገጥ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይደረጋል። ለሂደቱም መሳካት እያንዳንዱ ተባባሪ አካል በየወረዳው (ልዩ ወረዳው) ከሚገኙ መዋቅሮቹ አንድ ሰው ለየወረዳው ይወክላል። ኮሚሽኑም ይህንን ተግባር ለማከናወን የተለያዩ መመሪያዎችንና የሥልጠና ማንዋሎችን አዘጋጅቷል። የኮሚሽኑ አባላትና ሰራተኞችም ተባባሪ አካላት የተሰጣቸውን ሀላፊነትና አደራ በብቃት ለመወጣት እንዲችሉ ስልጠና ከመስጠት ባሻገር የቅርብ ክትትል ያደርጋሉ።